20ኛ ዓመት ቁጥር 4
20th Year No. 4

ባሕር ዳር ጥር 04 ቀን 2010 ዓ.ም
Bahir Dar, December 12, 2018

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State
## In the Federal Democratic Republic of Ethiopia

| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State | ✉ 1324<br>የአንዱ ዋጋ ...... BR<br>Unit Price Birr.......... |
|---|---|---|

| ማውጫ | Content |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 162/2010 ዓ.ም** | **Regulation No.162/2018** |
| የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የታክስ አስተዳደር ደንብ | **Council of the Amhara National Regional Government Tax Administration Regulation** |

**ደንብ ቁ ጥር 162/2010 ዓ.ም**

**በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም. መሰረት የወጣ የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የታክስ አስተዳደር ደንብ**

የክልሉ ታክስ አስተዳደር ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ በክልሉ የሚሰበሰቡ ሁሉም ታክሶች በወጥነት የሚመሩበትና ራሱን የቻለ የክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ የወጣ በመሆኑ

ይህን አዋጅ በክልሉ ውስጥ ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በጥቅል የሰፈሩ ጉዳዮችን በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

**Regulation No.162/2018**

**TAX ADMINISTRATION REGULATION OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL GOVERNMENT ISSUED PURSUANT TO TAX ADMINISTRATION PROCLAMATION NO.241/2016**

WHEREAS, it is necessary to enact a separate tax administration proclamation governing the administration of domestic taxes with a view to render the tax administration system more efficient, effective and measurable ;

In order to ensure the implementation of this Proclamation in the Regional State,

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ (7) ና በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም. አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የታክስ አስተዳደር አዋጅ ማስፈጸሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር_______/2010 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

ሀ/ "አዋጅ" ማለት የክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው፤

ለ/ "የተሻረው አዋጅ" ማለት የክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም. (እንደተሻሻለ) ነው፤

ሐ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

2 በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች እንደ አግባብነቱ በአዋጁ ወይም በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ዓ.ም. የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3 በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

**NOW, THEREFORE,** the council of the Amhara National Regional State, in accourdance with the powers vested in it under the provision of Article 58 sub-article 7 of the Revised Constitution of the National Region and Article 135 Sub Article 1 of the Amhara National Regional State Tax Administration Prolamation No-241/2016 hereby issued this Regulation..

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "The Regional Council of Regional Government Tax Administration Regulation No. --/2018

2. **Definition**

1. Unless the context requires otherwise, in this Regulations

a Proclamation" means the Amhara National Regional State Tax Administration Proclamation No. 241/2016;

b Amahara National Regional State Income Tax Proclamation 76/2002(as amended).

c Person" means a natural person or a juridical person.

2 Terms and phrases used in these Regulation shall have the same meaning as in the Proclamation or the Regional Government Income Tax Proclamation No.240/2016 , as the case may be,

3 Author of the masculine gender in this regulation shall include the feminine gender of any provision.

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

### 3. ምስጢራዊ መረጃ ስለመስጠት

የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ምስጢራዊ ሰነድ ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ጥያቄውን በጽሑፍ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም እርሱ ለሚወክለው ሰው ሲያቀርብና ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለምዝገባ

### 4 ማንነትን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ

1. ማንኛውም ግለሰብ ከሚያቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ከሚከተሉት የማንነት የሰነድ ማስረጃዎች አንዱን አብሮ ማቅረብ አለበት፤
   - ሀ/ ወቅታዊ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት የተረጋገጠ ቅጂ፣ ወይም
   - ለ/ የግለሰቡ ወቅታዊ የኢትዮጵያ የመንጃ ፈቃድ የተረጋገጠ ቅጂ፣ ወይም
   - ሐ/ የግለሰቡ የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ የተረጋጠ ቅጂ፣ ወይም
   - መ የግለሰቡ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ወይም
2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀተጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም

## PART TWO

## ADMINISTRATION OF TAX LAWS

### 3 Supply of Confidential Information

Without prejudice to Article 8(2) of the proclamation, the Authority shall provide a confidential document or information only when a written request is submitted to the Director General or his representative and the provision of the document or information is authorized.

## PART THREE

## REGISTRATION

### 4 Documentary Evidence of Identity

1 An application for registration by an individual shall be accompanied by any of the following documentary evidence of identity
   - a the individual’s current residence identity card or certified copy of the page of the Ethiopian or foreign current passport containing the individual's personal information; or
   - b certified copy of the individual’s current Ethiopian driver's licence ; or
   - c certified copy of the page of the individuals current foreign driver's licence containing personal information of the individual and to which the photograph of the individual is attached; or
   - d certified copy of the individual’s birth certificate

2 Notwithstanding the provision of sub article 1 of this article, the Authority

ባለስልጣኑ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሌላ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ እንዲያቀርብለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

3 በኩባንያ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኩባንያው የተቋቋመበትን ወይም የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

4 በሽርክና ማህበር የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከሽርክና ማህበሩ የምዝገባ ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

5 በሌላ በማናቸውም ድርጅት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከድርጅቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማናቸውም የመመስረቻ ወይም ማቋቋሚያ ሰነድ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

**5 የማንነት አካላዊ መረጃ**

1 ለግለሰብ ምዝገባ ዓላማ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ የግለሰቡን ትክክለኛ ማንነት ለማረጋገጥ፣ ወይም

ለ የማንነት ስርቆትን ወይም ማጭበርበርን ለመከላከል አመልካቹን ግለሰብ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2 ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ከግለሰብ ጋር በተገናኘ “የማንነት አካላዊ መረጃ” ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ የፊት ገጽታ መለያ፣

ለ የጣት አሻራ መለያ፣

ሐ የድምጽ መለያ፣

may require the applicant to submit such other evidence as it deems necessary.

3 An application for registration by an incorporated company must be accompanied by the certificate of incorporation or registration of the company.

4 An application for registration by a partnership must be accompanied by the partnership deed.

5 An application for registration by any other body must be accompanied by the certificate of registration, or other document of formation or creation.

## 5 Biometric Information

1 For the purposes of registration of an individual, the Authority may require an individual to submit biometric information so as to:

a ensure the proper identification of the individual; or

b Counteract identity theft or fraud.

2 In this Article, “biometric information”, in relation to an individual, means biological data to authenticate the identity of the individual, and may include the following:

a facial recognition;

b fingerprint recognition;

c vocal recognition;

መ የዓይን ክፍሎች (ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ፣

d iris or retina recognition.

## ክፍል አራት
## ስለታክስ እንደራሴዎች

## PART FOUR
## TAX REPRESENTATIVES

### 6 ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ

1 ለአዋጁ አፈጻጸም ኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት 'ወኪል' ተብሎ በሚጠራ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውነው የንግድ ሥራ ወኪሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የታክስ እንደራሴ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንደታክስ እንደራሴ የሚቆጠር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወኪል በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (40) መሠረት ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ ከሆነ ሌላ ማንኛውም ሰው ተጨማሪ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

### 6 Tax Representative of a Non-Resident

1 For a non-resident conducting business in Ethiopia through the activities of a person (referred to as the "agent') constituting a permanent establishment in Ethiopia of the non-resident under Article 4(4) of the Regional Income Tax Proclamation, the agent shall be a tax representative of the non-resident for the purposes of the Proclamation.

2 The treatment of an agent as the tax representative of a non-resident under sub-article (1) of this Article shall be in addition to any other person treated as the tax representative of the non-resident under Article 2(40) of the Proclamation

## ክፍል አምስት
## የከባድ ችግር ሁኔታዎች

## PART FIVE
## HARDSHIP CASES

### 7 ስለታክስ ምህረት ገደብ

ቢሮው በአዋጅ አንቀጽ 51 መሠረት የሚሰጠው የታክስ እና የዘገየ ክፍያ ወለድ ምህረት የገንዘብ ጣሪያ 100,000.(አንድ መቶ ሺህ) ብር ነው፡፡

### 7 Limit to Remission of Tax Debt

The maximum amount of tax debt and late payment interest that the Burea may remit under Article 51 of the Proclamation shall be 100,000 (One Hundred) birr.

## ክፍል ስድስት
## ስለቅጾችና ማስታወቂያዎች የታክስ ክፍያ

## PART SIX
## FORMS,NOTICES AND PAYMENT OF TAX

### 8 ስለሰነዶች አቀራረብና የታክስ አከፋፈል ሥርዓት

### 8 Manner of Filing Documents and Paying Tax

1 በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው የታክስ ማስታወቂውን ወይም ሌላ ማናቸውንም +ሰነድ በሚከተለው አኳሃን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፡፡

ሀ የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በማስተላለፍ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ክፍያ መፈጸም፣ ወይም

ለ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በአካል በማቅረብ ወይም በፖስታ ለባለሥልጣኑ በመላክ.

2 የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 3 ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ በታክስ ህግ መሠረት ሰነድ የማቅረቢያ ወይም ታክስ መክፈያ ጊዜ ወይም ሌላ ማናቸውም እርምጃ የሚወሰድባቸው ቀን ተከታታይ በዓላት ከሆኑ የሚቀጥሉት ተከታታይ ቀናት የሥራ ቀናት ይሆናል፡፡

9 ስለሰነዶች ማቅረቢያ እና የታክስ መክፈያ ቦታ

1 በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንኡሰ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር (ለ) መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ በላይ የንግድ ሥራዎችን የሚያካሂድ ወይም ቅርንጫፍ ያለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ገቢውን በአመነጨበት ክልል ሰነዶችን ማቅረብ ና ታክስ መክፈል አለበት፡፡

2 በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንኡሰ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር (ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሰራ

1 Except as otherwise provided in the Proclamation or these Regulations, a person shall file a tax declaration or other document with the Authority and pay tax in the following manner:

a when Article 82(2) of the Proclamation applies, by electronic transmission or payment in accordance with the directions of the Authority under that Article; 81(2) or

b in any other case, by personal delivery or post to an office of the Authority.

2 Article 75 sub article 3 of the Proclamation is applicable if the date of delivery of a document, taxpayer's time or any other action is a continuous consecutive calendar day, shall be the following consecutive working days.

## 9 <u>Place for Filing of Documents and Payment of Tax</u>

1 When Article 8 Sub Article 1(b) applies to a resident of Ethiopia that has more than one business or branch office in Ethiopia, the resident shall file documents and pay tax at the Region where he derived most of his income.

2 When Article 8 Sub Atticle 1(b) applies to a non-resident conducting business through a

ድርጅት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ ገቢውን በአመነጨበት ክልል ሰነዶችን ማቅረብና ታክስ መክፈል አለበት፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)ና (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም የክልል ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ ገቢውን ማስታወቅ ያለበት ገቢውን ላመነጨበት ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የግብር አስገቢ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

4 ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ባለስልጣኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል

**ክፍል ሰባት**
**ስለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን**
**ምዕራፍ አንድ**
**ኮሚሽኑ በይግባኝ ክርክር ሂደት ያለው ሥልጣን**

**10 የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ስለማቋቋም**

1 ለክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 85 ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ሲባል በከተሞች እና በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንደአስፈላጊነቱ ሊቋቋም ይችላል።

2 የዚህ አንቀጽ ንኡሰ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ከሚቋቋምባቸው ከተሞች ውጭ ባሉ ከተሞች እና ወረዳዎች በሥራ ላይ ያለው የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

3 ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1 እና 2) ድንጋጌዎች አፈጻጸም ባለስልጣኑ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ

permanent establishment in Ethiopia, the non-resident shall file documents and pay tax at the Region where the main operations of the permanent establishment take place.

3 Notwithstanding the provision of this Article Sub Article 1 and 2 a regional tax payer who operates businesses with alicenses issued by more than one regional states or urban administration shall declare his income and pay the tax there on, to derived income of each Regional State or Urban Administration

4 The Authority may issue directives for the implementation of the provisions of this Article

**PART SEVEN**
**TAX APPEAL COMMISSION**
**CHAPTER ONE**
**POWERS OF THE COMMISSION ON A HEARING**

**10 Establishment of the Tax Appeal Commission**

1 According to the provisions of Article 85 sub article (1) of the Proclamation, the tax appeals commission may be established in Urban and other place of the region.

2 Without prejudice to the provisions of sub-Article (1) of this Article, the due process hearing will be held in towns and districts outside the cities where the Tax Appeal Commission will be established.

3 The authority may issue a detailed directive for the performance of sub-

ይችላል፡፡

## 11 የኮሚሽኑ ሥልጣን

1 ኮሚሽኑ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ በቃለ- መሃላ ወይም በማረጋገጫ የተደገፈ ማስረጃ መቀበል፣

ለ የዚህ ደንብ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስለክርክሩ ሂደት ተገቢው ማስታወቂያ ደርሶት ያልቀረበ ወገን ቢኖር በሌለበት ክርክሩን ማስቀጠል፣ ወይም

ሐ የክርክሩን ሂደት በቀጠሮ ማሳደር ወይም ማስተላለፍ ፡

2 የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የክርከር ሂደት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

3 በኮሚሽኑ የክርክር ሂደት እንደምስክር ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ሰው በኮሚሽኑ መመሪያ መሠረት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚጠራው ምስክር የሚከፍለውን ያህል የውሎ አበል ክፍያ ይፈጸምለታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለኮሚሽኑ ውሳኔ

## 12 የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቋረጥ፣ ስለመዘጋት ወይም እንደገና ስለማየት

1 ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለኮሚሽኑ ያቀረበውን ይግባኝ በማናቸውም ጊዜ ለኮሚሽኑ ሬጅስትራር የጽሑፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ማቋረጥ ወይም መተው የሚችል ሲሆን፣ ኮሚሽኑም ይህ በሚሆንበት ጊዜ ይግባኙን ይዘጋል፡፡

2 የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው



articles (1 and 2) of this Article.

## 11 Powers of the Commission

1 The Commission shall have the following specific powers and duties subject to this regulation.

a take evidence on oath or affirmation;

b subject to Article 12(2) of this Regulation, proceed in the absence of a party who has had reasonable notice of a hearing; or

c adjourn a hearing from time to time.

2 The President of the Commission may summon a person to appear before the Commission at a hearing to give evidence.

3 A person summoned to appear as a witness before the Commission shall be entitled to be paid fees at such rates as are allowable for witnesses in the High Court in accordance with the directive of the Commission.

## CHAPTER TWO

## DECISION OF THE COMMISSION

## 12 Discontinuance, Dismissl or Reinstatement of Appeal Application

1 An appellant may discontinue or withdraw an appeal to the Commission at any time by filing written notice with the Registrar of the Commission and the Commission shall dismiss the appeal

2 If an applicant fails to appear in person

በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት በአካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሳይቀረብ የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡

3 የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከይግባኙ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ፕሬዝደንቱ ስለኮሚሽኑ ሆኖ ይግባኙን መዝጋት ይችላል፡፡

4 ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት ይግባኝ የዘጋ እንደሆነ፣ ይግባኝ ባዩ የይግባኙ መዘጋት ማስታወቂያ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኙ እንደገና እንዲታይለት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል፡፡

5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፣ በፕሬዚደንቱ የሚሰጠው ሌላ ትዕዛዝ ቢኖር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ይግባኙን እንደገና ሊያይ ይችላል፡፡

## 13 በተከራካሪ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ስምምነት

በይግባኙ ስሚ ማናቸውም ደረጃ ከይግባኙ ወይም ከይግባኙ ከፊል ጉዳይ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ ስለሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ የተስማሙ እንደሆነ፡-

1 ስምምነት የተደረሰው ኮሚሽኑ ከሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ ሲሆን ፣ ኮሚሽኑ በሁኔታዎቹ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2 ስምምነት የተደረሰው በይግባኙ ከፊል ጉዳዮች ላይ እንደሆነ፣ ኮሚሽኑ በይግባኙ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የስምምነቱን ሁኔታዎች ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል፡

## 14 ለባለስልጣኑ ስለሚመለስ ውሳኔ

or be represented at a hearing of the Commission, the Commission may dismiss the appeal.

3 If an applicant fails to comply with the direction of the commission in relation to the appeal under consideration, the President may, on behalf of the Commission, dismiss the appeal.

4 If the Commission has dismissed an appeal under sub-article (2) or (3) of this Article , the appellant may, within 30 days after receiving notification that the appeal has been dismissed, apply to the Commission for reinstatement of the appeal.

5 If an application has been made under sub-article (4), the Commission may reinstate the appeal subject to any directions made by the President.

## 13 Agreement Between the Parties

If at any stage during an appeal, the parties agree in writing as to the terms of a decision of the Commission on the appeal or on a decision relating to part of the appeal:

1 the Commission may make a decision in accordance with the terms of the agreement where the agreement relates to the terms of the decision of the Commission.

2 the commission may give effect to the terms of the agreement where the agreement reached relates to a decision on part of the appeal.

## 14 Decision to be Remitted to the Authority

1 ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ 90 መሠረት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ እንደገና እንዲመለከተው ለባለሥልጣኑ ሲመልስ፣ ባለሥልጣኑ ኮሚሽኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ከግምት በማስገባት፣

ሀ ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ሊያጸና፣

ለ ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ሊያሻሽል፣ ወይም

ሐ የአዋጁ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የታክስ ስሌቱን ከፍ ማድረግን ጨምሮ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

2 ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ የሚቀርብበትን ውሳኔ ሲያሻሽል ወይም አዲስ ውሳኔ ሲሠጥ የተሻሻለው ወይም የተሰጠው አዲስ ውሳኔ በኮሚሽኑ በይግባኝ እየታየ እንዳለ ይግባኝ የሚቀርብበት ውሳኔ የሚቆጠር ሲሆን፣ ይግባኝ ባዩ ደግሞ ባቀረበው ይግባኝ ሊቀጥል ወይም ይግባኙን ሊያነሳ ይችላል፡፡

## 15 ውሳኔዎችን ስለማረም

1 ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሠረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ወይም ሊያርም ይችላል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሻሻለው ይዘት በኮሚሽኑ እንደተሰጠ ውሳኔ ይቆጠራል፡፡

1 If, in accordance with Article 90 of the Proclamation, the Commission remits an appealable decision to the Authority for reconsideration, the Authority may, taking in to account the directions of the Commission:

a affirm the appealable decision;

b vary the appealable decision; or

c set aside the appealable decision and make a new decision, including increasing a tax assessment when Article 90 (6) applies.

2 When the Authority varies or sets aside an appealable decision in accordance with sub-article (1) of this Article , the decision as varied, or the new decision, shall be taken to be the appealable decision that is the subject of the appeal before the Commission and the appellant may either proceed with or withdraw the appeal.

## 15 Correction of Decision

1 The Commission may alter the text of a decision or written statement of reasons for a decision if satisfied that there is an error in the text of the decision or the written statement of reasons.

2 The altered text under sub-article (1) of this Article shall be treated as the decision of the Commission.

3 ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፣

ሀ የህትመት ወይም የአጻጻፍ ስህተትን፣ ወይም

ለ በአንድ ውሳኔና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይን ማናቸውንም አለመጣጣም ይጨምራል፡፡

**ምዕራፍ ሦስት**

**ስለኮሚሽኑ አስተዳደር**

**16 ክርክር ስለሚካሄድበት ቦታ**

የኮሚሽኑ የክርክር ስሚዎች የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት በሚወስነው ቦታ ይካሄዳሉ፡፡ ስለሆነም ስሚ የሚካሄድበትን ስፍራ ኮሚሽኑ ለተከራካሪዎች ማሳወቅ አለበት፡፡

**17 ስለክርክሩ ወጪዎች**

ተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ሂደት ያወጡትን ወጪን በሚመለከት ኮሚሽኑ ተገቢና ምክንያታዊ መስሎ የሚታየውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**18 ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ስለማቅረብ**

ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚገባው ማናቸውም ሰነድ በኮሚሽኑ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት፡፡

**19 ሰነዶች ስለሚሰጡበት አድራሻ**

ይግባኝ ባይ ከይግባኙ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ማናቸውም ሰነድ አድራሻውን በጽሑፍ ማስታወቂያ ለሬጅስትራሩ መስጠት አለበት፡፡

**ክፍል ስምንት**

**ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት**

**20 የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁና ተስማሚ ስለመሆን**

3 For the purpose of this Article, an error in the text of a decision or statement of reasons includes

a a typographical or clerical error; or

b any inconsistency between the decision and the statement of reasons.

**CHAPTER THREE**

**ADMINSTRATION OF THE COMMISSION**

**16 Place of hearing**

The hearings of the Commission shall take place at a location to be designated by the President of the Commission. Accordingly, the commission shall notify the parties the place of the hearing.

**17 Costs**

The Commission may make such order as it considers fair and reasonable regarding costs incurred by the parties in relation to the proceeding

**18 Filing of Documents with Commission**

Any document required to be filed with the Commission shall be filed at the Registry of the Commission.

**19 Address for Service of Documents**

An appellant shall give the Registrar written notice of the appellant's address for service of any documents relating to the appeal.

**PART EIGHT**

**LICENSING OF TAX AGENTS**

**20 Fit and Proper Person to Provide Tax Agent Services**

1 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)ና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ከተገኘ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁና ተስማሚ እንደሆነ ሰው ይቆጠራል፡

ሀ በታክስ፣ በሂሣብ አያያዝ፣ በንግድ ሥራ፣ በሕግ ፣በሥራ አመራር ፣በምጣኔ ሀብት ወይም በሌላ በማናቸውም ተመሳሳይ የትምህርት መስክ ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ማስረጃ ያለው እንደሆነና

ለ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት፣

1. ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር ሆኖ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት፣ ወይም
2. እንደታክስ ሠራተኛ በማገልገል የሁለት ዓመት የሙሉ ጊዜ የሥራ ልምድ ያለው እንደሆነ፡፡

2 አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) ከተመለከተው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ልምድ በሌላ ሀገር ያገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ግለሰቡ የዚህም አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)(1) መስፈርትን እንዳሟላ አድርጎ ሊወስደው ይችላል፡፡

3 የሚከተሉት ግለሰቦች የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁና ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው አይቆጠሩም፡፡

ሀ ዕዳውን መክፈል ያልቻለ ወይም መክሰሩ በፍርድ የተረጋገጠ ግለሰብ፣

1 Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article , an individual is a fit and proper person to provide tax agent services if the individual has:

a qualification of at least first degree in taxation, accounting, business, law, economics, management or other similar discipline; and

b has at least 2 years of full-time experience in the previous 5 years in Ethiopia:

1. in providing tax agent services under the supervision of a licensed tax agent; or
2. as a tax officer.

2 The Authority may regard an individual as satisfying sub-article (1)(b)(1) of this Article if the individual has experience equivalent to that specified in sub-article (1)(b)(1) of this Article in another jurisdiction.

3 The following individuals are not regarded as a fit and proper person to provide tax agent services:

a an individual who could not discharge his debt or who is a judicially declared bankrupt;

ለ በስነምግባር ጉድለት በሙያ ማህበሩ አማካኝነት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ፣

ሐ ከእምነት ማጉደል ጋር በተገናኘ ወንጀል በፍርድ ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠና ቅጣቱን ፈጽሞ ያልተሰየመ ግለሰብ፣

መ በተሻረው አዋጅ መሠረት ጭምር የታክስ ግዴታውን ያለመወጣት ሪከርድ ያለበት ግለሰብ፣

4 ለዚህ ደንብ አንቀጽ 20 አፈጻጸም ባለስልጣኑ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21 የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1 በተሻረው አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው "የቀድሞ ኮሚሽን" ተብሎ ለሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የተሾሙ አባላት አገልግሎት በአዋጁ መሠረት "አዲስ ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር ይቋረጣል፡፡

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚመለከተው ሰው በአዋጁ አንቀጽ 86 መሠረት ለአዲሱ ኮሚሽን አባልነት ለመታጨት ብቁ ይሆናል፡፡

3 በአዋጁ አንቀጽ 86 ንኡስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ቁጥር (ለ) "የታክስ ሕግ" በሚል የተጠቀሰው የተሻረውን አዋጅ ይጨምራል፡፡

4 ለቀድሞው ኮሚሽን የቀረበ ይግባኝ ኮሚሽኑ ሥራውን ከማቆሙ በፊት ውሳኔ ያላገኘ እንደሆነ፣ የአዲሱ ኮሚሽን ፕሬዚደንት የሚሰጠው

b an individual who has been found guilty of misconduct by a professional body;

c an individual who has been convicted of a criminal offence relating to dishonesty and who has not been reinstated

d an individual who has an unsatisfactory tax compliance record including under the repealed Proclamation.

4 The authority may issue a detailed directive for the implementation of the provisions of Article 20 of this Regulation.

## PART NINE

## MISCELLANEOUS

### 21 Transitional Regulations

1 The appointment of a person as a member of the Tax Appeal Commission established under the repealed Proclamation (referred to as the "former Commission") shall terminate once the Tax Appeal Commission established under the Proclamation (referred to as the "new Commission") comes into operation.

2 A person to whom sub-article (1) of this Article applies shall be eligible for appointment as a member of the new Commission in accordance with Article 86 of the Proclamation.

3 The reference in Article 86(3) (b) of the Proclamation to a "tax law" shall include the repealed Proclamation.

4 If an appeal was filed with the former Commission and the appeal was not finalised before the former Commission ceased operations, the

ማናቸውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኙ በአዲሱ ኮሚሽን ከታየ በኋላ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

appeal shall be decided by the new Commission subject to any directions that the President of the new Commission may make.

**22 መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1 ቢሮው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ በዚህ ደንብ ተለይተው በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**23 ደንቡ ስለሚጸናበት ቀን**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**

**ጥር 4 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ገዱ አንዳርጋቸው**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

**ርእሰ መስተዳድር**

## 22 Power to issue Directives

1 The Burea may issue Directives for the proper implementation of these Regulations.

2 The Authority without prejudice to the provisions of Article 1 of this Article may issue directives on the issue by this Regulation.

**23 Effective Date**

This Regulation shall enter in to force on the date of its publication in the Regional Zikre-Hig Gazzettee.

**Done at Bahir Dar**

**This 12th day of January,2018**

**Gedu Andargachew**

**President of Amhara National Regional State**